**“ግርዛት (FGM) ልማድ እና ባሕል ነው – መፈፀም እንዳለበት የሚገልፁ ኃይማኖታዊ ፅሑፎች የሉም”**

## ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት ለሆኑትስ፥ እንዴት ሊረዱ ይችላሉ?

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት ለሆኑት ድጋፍ የሚገኘው በ  በኩል በUCLH የሕፃናት ሕክምና አገልግሎት ነው። ለክሊኒክ ቀጠሮ መያዝ የሚቻለው በ **UCLH.paediatricsafeguarding@nhs.net** በመላክ ነው።

## ክሊኒካችንን ይጎብኙ

NFGMSC   Summerfield Women’s Clinic

**የመክፈቻ ጊዜ**

9am-5pm

**አድራሻ**

Summerfield Primary Care Centre,
Heath Street, Birmingham, B18 7AL

**ስልክ ቁጥር**

07989209483

**ለመተላለፍ ኢ-ሜይል ያድርጉ**

swbh.summerfieldfgm@nhs.net

ለክሊኒኮቹ ሙሉ ዝርዝር ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፥ እባክዎን ይህንን ይጎበኙ፡ **www.nhs.uk/fgm**

**#FGMQUESTIONS**
**#NFGMSC**
**#ENDFGM**

## ብሔራዊ የሴት ግርዛት ድጋፍ ክሊኒኮች (National Female Genital Mutilation Support Clinics) – ምንድን ናቸው?

ብሔራዊ የሴት ግርዛት ድጋፍ ክሊኒኮች (NFGMSC) ማህበረሰብ ተኮር ክሊኒኮች ሆነው ለተገረዙት ሴቶች ሁለንተናዊ እንክብካቤ ሞደልን ለሴቶች (18 ዓመት +) ለሆኑት ያቀርባል። በሚከተሉትን የተለያዩ ሙያ ባላቸው ሴት ቡድን አማካይነት የሚሰጠውን ብዙ ዓይነት ያገልግሎቶችን ድጋፍ ያቀርባሉ፤

- አካላዊ ምርመራንና ሕክምናን (አስፈላጊ ከሆነ የግርዛት ጠባሳን በቀዶ ጥገና ማከምን ጨምሮ)፤
- የስነ-ልቦና ድጋፍ/ምክር፤
- አጠቃላይ መረጃ፤
- ከFGM የጤና ተሟጋቾች ጋር የመገናኘት ዕድል ያገኛል፥ እንደዚሁም፥
- ተጨማሪ ክትትል የሚያስፈልግ ከሆነ ለልዩ ባለሙያ አማካሪ ቀጣይ ድጋፍ።

ክሊኒኮቹ በእያንዳንዱ አራቱም ክልሎች ውስጥ እንድገኙ ይደረጋሉ፡ ሴሜን ኢንግላንድ፥ ሚድላንድስ እና ምስራቅ፥ ለንደን እና ደቡብ ክልል።


ብሔራዊ የሴት ግርዛት ድጋፍ ክሊኒኮች (NFGMSC) ሴቶች ስለጤናቸው ፍላጎቶች አንገብጋቢ በሆነና ፈራጅ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ተጋብዘው የሚወያዩበትን አካባቢ ይፈጥራል። ይሄኛው ሴቶች እራሳቸውን ማስተላለፍ የሚችሉበት ፈጣን አገልግሎት ቢሆንም በአጠቃላይ ሐኪሞችና ሌሎች የጤና ማለሙያዎች እንዲተላለፉ መደረጉ ግን እጅጉን የሚበረታታ ነው።

በቀጠሮሽ ጊዜ የግርዛቱን (FGM) ዓይነት መመርመር እንችላለን። በክሊኒካችን ውስጥ በሚገኘው የአከባቢ ማደንዘዣ በመጠቀም የግርዛትን ጠባሳ በቀዶ-ጥገና ሕክምና (‘ወደነበረበት መመለስ/መክፈት’ ሕክምና) እንሰጣለን፥ ወይም ደግሞ ሕክምናው በተመረጠና አጠቃላይ ማደንዘዣ የሚደረግ ከሆነ ሆስፕታል ውስጥ በሚገኘው ወደ ልዩ አማካሪ ልናስተላልፍዎ እንችላለን። ከማሕፀናቸው በታች ከፍተኛ ሕመም ያለባቸው ወይም የመሽናት ችግር ያለባቸው ሴቶች ለሽንት ስርዓት ችግር ሕክምና አገልግሎት ባለሙያ ይተላለፋሉ።

ML6055

NHS

# Summerfield Women’s Clinic




ብሔራዊ የሴት ግርዛት ድጋፍ ክሊኒኮች (NFGMSC) ባህበረሰብ ተኮር ክሊኒኮች ሆነው ለተገረዙት ሴቶችና እርዳታን በሚሹበት ወቅት ነፍሰ-ጡር ላልሆኑት ሁለንተናዊ እንክብካቤ የሚያቀርብ ነው። በሚከተሉትን የተለያዩ ሙያ ባላቸው ሴት ቡድን አማካይነት የሚሰጠውን ብዙ ዓይነት ያገልግሎቶችን ድጋፍ ያቀርባሉ፤ አካላዊ ምርመራንና ሕክምናን (አስፈላጊ ከሆነ የግርዛት ጠባሳን በቀዶ ጥገና ማከምን ጨምሮ)፤ የስነ-ልቦና ድጋፍ/ምክር፤ አጠቃላይ መረጃ፤ እና ከFGM የጤና ተሟጋቾች ጋር የመገናኘት ዕድል ያገኛል፥ እንደዚሁም።

ተጨማሪ ክትትል የሚያስፈልግ ከሆነ ለልዩ ባለሙያ አማካሪ ቀጣይ ድጋፍ ይኖራል። ክሊኒኮቹ በእያንዳንዱ አራቱም ክልሎች ውስጥ እንድገኙ ይደረጋሉ፡ ሰሜን ኢንግላንድ፥ ሚድላንድስ እና ምስራቅ፥ ለንደን እና ደቡብ ክልል።

## የሴት ግርዛት ምንድን ነው?

**የሴት ግርዛት (FGM) ማለት ያለምንም እንዲከናወን የሚያስገድድ የሕክምና ምክንያት በሌለበት ሆን ተብሎ የሴት ልጅን ብልት መቁረጥ፥ መጉዳት ወይም መቀየርን የሚያስከትል ሂዴት ነው።**

እንደዚሁም ደግሞ “ፊሜል ስረካምሲሽን” ወይም “መቁረጥ” እናም በሌሎች ቃላቶችም ጉድኒን፥ ሱና፥ ሓላላይስ፥ ቆዲን፥ ኪታን፥ ታራ፥ ኢቢ ሁግዊ፥ ክፋድ፥ ታሆር፥ ኣብሱም፥ መገረዝ፥ ቦንዶ፥ ኩታሂሪ፥ መካንሻብ፥ፋናዱ ዲ ሚንጀር፥ ኩያንጎ፥ እና ኒአካ።

- FGM ብዙውን ጊዜ ከጨቅላነት ዕድሜ እስከ 15 ዓመት ባሉት ታዳጊ ሴት ልጆች ላይ ሲሆን፥ ባብዛኛው የኮሮዳነት ዕድሜ ከመጀመሩ በፊት ነው።
- ይህ ተግባር የሕፃናት መብት ጥሰትና በUK ውስጥ ሕገ-ወጥ ነው።
- FGM የሴቶችንና የልጃገረዶችን ሰብአዊ መብቶች ይጥሳል።
- ግርዛት (FGM) ልማድ እና ባሕል ነው – መፈፀም እንዳለበት የሚገልፁ ኃይማኖታዊ ፅሑፎች የሉም።
- በጣም የሚያምና በሴቶችና ልጃገረዶች ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ተግባር ነው። የረጅም ጊዜ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ችግር፥ መሃንነት፥ ልጅን የመውለድ ችግርና የአዕምሮ ጤና እንከንን ለረጅም ጊዜ ሊያስከትል ይችላል።

ግርዛት (FGM) ካለብሽ ወይም የሆነ ሰው በዚህ ችግር ገጥሞት ብሎ ያሳሰበሽ እንደሆነ እርዳታና ድጋፍ ይኖራል።

## የተለያዩ የግርዛት (FGM) ዓይነቶች ምን ናቸው?

**ዓይነት 1:** ቅንጥርን እና/ወይም ሸለፈቱን በክፊል ወይም በሙሉ ማስወገድ (ኪሊቶረይደክቶሚ)።

**ዓይነት 2:** ቅንጥርን እና የብልት ትናንሽ ከንፈሮችን ከትላልቆቹ ከንፈሮች ጋር ወይም ከእነሱ ውጪ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድ።

**ዓይነት 3:** ቅንጠርን በመቅደድ ወይም ሳይቀዱ በሚሆኑት (ኢንፍቡለሽን) ዜዴ የብልት ትናንሽ ከንፈሮችን እና/ወይም ከትላልቆቹ ከንፈሮችን በመቁረጥና በማጠፍ የሴት ብልት ቀዳዳን የሚዘጋ በማበጀት ማጥበብ።

**ዓይነት 4:** ሌሎች ሁሉም ከሕክምና ዓላማ ውጪ ለሆኑት በሴት ብልት ላይ የሚደረጉ፥ ለምሳሌ፥ መውጋት፥ ቀዳዳ ማበጀት፥ መቁረጥ፥ መቦደስ እና ማደንዘዝ።

## የሕክምና እንክብካቤ


ተገርዘሽ ከሆነ ሊያጋጥሙሽ የሚችሉት አካላዊ ችግሮች የሚሆኑት እንደ:

- የሽንት ስርዓት ኢንፌክሽን።
- የሴት ብልት ኢንፌክሽን።
- ሕመም ያለበት የወር አበባ።
- ሕመም ያለበት ግብረ-ስጋ ግንኙነት።
- የሐዘን ስሜት፥ ፍርሃት ወይም ድብርት።
- ልጅን በሚወለድበት ጊዜ የሚከሰቱ ችግኦች።

## የስነ-ልቦች እንክብካቤ

ተገርዘሽ ከሆነ እነዚህና የመሳሰሉት የስነ-ልቦና ችግሮች ይገጥሙሻል፡

- ወደ ኃላ ተመልሰሽ የተገረዝሽበትን ማስታወስ።
- ድብርት።
- ፍርሃት።
- ጭንቀት።
- መጥፎ ህልሞች።
- ዝቅተኛ በራስ መተማመን።
- ሌሎች የአህምሮ ጤና ችግሮች።



## የመብት ድጋፍ

በእነዚህ ጉዳዮች ድጋፍ ሊያደርግ በሚችለው በግርዛት ጤና መብት (FGM Health Advocate) ድጋፍ ማግኘት ትችያለሽ፡

- ሚቾት እንዲሰማሽ ማድረግ።
- ማግኘት የሚትችይውን አገልግሎትና እንክብካቤ እንደዚሁም ድጋፍ እንዲትገልጪ መደገፍ።
- አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ላይ ላንች መተርጎም።
- በአንቺ ቦታ በመሆን ስለሌች መብት ያንቺ ፍላጎት ስለመተግበር መናገር።

## FGM እና የUK ሕግ

በUK ውስጥ፥ የህግ ጥሰት ነው:

- ለማንኛውም ግርዛትን (FGM) ለማካሄድ።
- ግርዛትን (FGM) ለማካሄድ በUK ውስጥ የሚኖሩትን ልጃ-ገረዶችን ወይም ሴቶችን ወዴ ሌላ ሀገር መውሰድ።
- የሆነ ሰው ግርዛት (FGM) እንዲታካሄድ መደገፍ (ይህም ጉዞን ማመቻቸትን ይጨምራል)። በግርዛት ሕግ( FGM Act 2003) ወንጀለኛ የሆነ ሰው እስከ 14 ዓመት እሰራት በሚደርስ ቅጣት ሊቀጣ ይችላል።
- ከወሊድ በኋልም ሴቶችን መስፋትም ሕገ-ወጥ ነው፥ ይህ ደግሞ ሪ-ኢንፉቡለሽን በመባል ይታወቃል።

> **“ግርዛት (FGM) የጤና ጥቅሞች የሉትም – ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል”**

## ነፍሰ-ጡር የሆነ ሴቶችስ፥ እንዴት ሊረዱ ይችላሉ?

ግርዛትን (FGM) ያደረጉ ሴቶቻችሁ ድጋፍ በአከባቢው ሆስፕታል የእናቶች መምሪያ በኩል ይገኛል።